# ገጸ በረከት — ለ«ሚሌንየም»

## ፩. ትናንት

ዕድሜው በግምት አስር ዓመት ቢሆን ነው። የያዛቸውን ሁለት ያረጁና የሸቦ ማንጠልጠያዎች ያሏቸውን ተለቅ ተለቅ ያሉ ጣሳዎች አንዱን በቀኝ እጁ ሌላውን በግራው ተሸክሞ እየተንገዳገደ አቀበቱን ለመውጣት ይታገላል። እያንዳንዱ ጣሳ በግምት አስር ሊትር ውሃ ቢይዝ ነው። ሸክሙ እንደከበደው ያስታውቃል። ጣሳዎቹ ከሁለት ወገን ተበስተው የገቡላቸው የሸቦ ማንጠልጠያዎች ጣቶቹን እየሰረሰሩ እንዳሳመሙት ከፊቱ ለማንበብ አያስቸግርም። ያለዕድሜው ብዙ የተጓዙት ባዶ እግሮቹ እንቅፋትና እሾህ ብዙ ያጠቃቸው፥ ነገር ግን ችግር ያጠጠራቸው መሆናቸው ያስታውቃል። እየተንገዳገደ አቀበቱን ሲወጣ ከረባዳዋ የምንጭ ጉድጓድ ቀድቶ ጣሳዎቹ ውስጥ የሞላው ውሃ በጥቂቱ መፍሰሱ አልቀረም። ፈጠን ባሉ ርምጃዎች የምንጩን ግርግር ካለፈ በኋላ የተደለላደለ ቦታ ፈልጎ ጣሳዎቹን ረጋ ብሎ አቧራማው መሬት ላይ አሳረፋቸው። የውሃው ክብደትና ሽቦዎቹ ማንጠልጠያዎች ያሳመሙትን እጆቹን እርስበርሳቸው እያፋተገ በርክክ ብሎ ጣሳዎቹን መመልከት ጀመረ —ከፊቱ የቀረበለትን ፈተና በአትኩሮት እንደሚመለከት ተማሪ።

መጀመሪያ አልገባኝም፤ ቀስ እያለ ነበር ምን እያደረገ እንደነበር የተገለጸልኝ። የጣሳዎቹ መክበድና የአቀበቱ ምቹ አለመሆን በሸክሙ ላይ ያስከተለው ንቅናቄ ምን ያህል የጣሳዎቹን ውሃ እንዳጎደለበት ነበር ተንበርክኮ በዐይኑ የሚለካው። ከምንጩ ፈንጠር ብዬ ከቆምኩበት ቦታ የልጁን ፊትና እንቅስቃሴ አጠና ጀመር። እርሱ አያየኝም እኔ ግን በተመስጦ አየዋለሁ። ለእርሱ የዕለት ተዕለት የፍዳ ኑሮ፥ ለእኔ ደግሞ አስገራሚ የሕይወት ድራማ። እየገረመኝ አየሁት። እንደተንበረከከ የጣሳዎቹን መጉደል እጆቹን እያፋተገ ያጤናል። እኔም አየዋለሁ — በመገረም። የጣሳዎቹ ያን ያህል መጉደል እንዳላስደሰተው ያስታውቃል። ለአንድ አፍታ ዐይኖቹን ከጣሳዎቹ ወደ ምንጩ ወርወር አድርጎ ተመለከተ። መልሶም ወደ ጣሳዎቹ፤ ከዚያም እንደገና ወደ ምንጩ . . . መልሶ ወደ ጣሳዎቹ . . . ከሕሊናው ጋር ሙግት እንደገጠመ ገባኝ። «ተመልሼ ጣሳዎቹን ልሙላቸው?» ከሚል ጥያቄ ጋር የሚታገል መሰለኝ። «እንደገና ተጋፍቼ?» . . . ሌላ ተቃራኒ ጥያቄ። ምንጩን ከቦ ከሚተራመሰው ሰውና ከብት ጋር ተጋፍቶ ጣሳዎቹን መሙላት? አልመሰልህ አለው። ትኩር ብዬ እያየሁት ነው። አሁንስ በመገረም አልነበረም። ልቤን ሐዘን ሲያከብደው ተሰማኝ። ዝም እንዳልኩ ከቆምኩበት መመልከቴን ግን ቀጠልኩ። ለመጨረሻ አንድ ጊዜ ወደ ምንጩ ተመለከተና ራሱን ነቅነቅ አድርጎ እጆቹን እያፍታታ ከተንበረከከበት ብድግ ብሎ ጣሳዎቹን እኩል አንዱን በግራ እጁ ሌላውን በቀኝ እጁ በጥንቃቄ አንስቶ ፈጠን ባለ ርምጃ መንገዱን ጀመረ። «ነገ ግን አንዲት ጠብታ ውሃ አላባክንም» የሚል የተስፋ ቃል ፊቱ ላይ ያነበብኩ መሰለኝ።

ረጅም ጉዞ ከፊቱ ይጠብቀዋል። ወዴት ይሆን የሚጓዘው? ለምንጩ ቅርብ ወደሚባለው መንደር የሚያስኬደው እጅግ አስቸጋሪ መንገድ ከግማሽ ሰዓት በላይ እንደሚወስድ ተነግሮኛል —

በመኪናᎁ ከመኪናም በላንድሮቨር ወይም በላንድክሩዘር። ምን ያህል ሰዓት ሊጓዝ ይሆን? እኩለ ቀን ሊሆን ነው። የፀሐዩቱ ጉልበት እንዳያሸንፈው የርምጃውን ፍጥነት ጨመር አድርጎ መንገዱን ተያያዘው። ጀርባውን ወደኔ ፊቱን ወደ ፀሐይ መጥለቂያ አቅጣጫ አዙሮ ውሃውን ከመደፋት፥ ባዶ እግሩን ከእንቅፋት እየተከላከለ ጉዞውን ቀጠለ። ከቆምኩበት ቦታ እየራቀም ሲሄድ ዕንባ ባቀረሩት ዐይኖቼ ተከተልኩት. . . ውሃ ቀጂውን ትንሽ ልጅ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ሲዳሞ ውስጥ ሚዳሶዱ በምትባል የገጠር መንደር ከምትገኝ የምንጭ ውሃ ዳር ሆኜ ነበር ልጁን ያስተዋልኩት — እንደፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በጥር ወር 2003 ዓመተ ምሕረት። ልጁን ያስተዋልኩባቸውን እነዚያን ጥቂት ደቂቃዎች ባሰበኩ ቁጥር የአገራችንን ችግሮች አስከፊነት፥ የድኅነቷን ጥልቀትና በተለይም ደግሞ የሕፃናቷንና የሴቶቿን የስቃይ ሕይወት እንዳስብ ያስገድዱኛል። ካለፉት ሠላሳ ዓመታት ወዲህ በሚሊዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተደጋጋሚየረሀብ አደጋና እልቂት ሲዳረግ የረሀቡ ድግግሞሽ የዜናውን አስቸኳይነትና አስደንጋጭነት ሳይቀንሰው አልቀረም። ረሀብ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የተለመደ ክስተት እየሆነም የመጣ ይመስላል። ነገር ግን በሚሊዮኖች እየተሰላ ተራብ የሚባለው ሕዝብ በደፈናው ስታትስቲክስ ብቻ ሆኖ እንዳይቀር ኢትዮጵያዊነታችን ስለሚያስገድደን በትንሹም ቢሆን ስለችግሩ ማሰባችን አልቀረም። ዘንድሮም የረሀብ አደጋው በሚሊዮኖች ላይ እያንዣበበ ነው።

ግን ለምን ይሆን ከዚህ የረሀብ አዙሪት ውስጥ ልንወጣ ያልቻልነው? በእርግጥ ራሳችንን መመገብ የማንችል ሰዎች ሆነን ነው? ተፈጥሮ በድሎን ነው? የረሀብ አደጋ ደርሶብን የማያውቅ ኢትዮጵያውያንስ የሚራበውን ወገናችንን በጅምላ ከማየት ባሻገር ረሀብ በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ የሚያደርሰውን ሰቆቃ ለመገመት አስበናል? የሚራብ ወገናችንንና የረሀብንስ ፊት በዐይነ ሕሊናችን ለመመልከት ሞክረናል? የረሀብን ኢትዮጵያዊ ገጽታ፥ የረሀብን ኢትዮጵያዊ ፊት ማለቴ ነው። አዎ፥ ረሀብ ፊት አለው። የሰው ፊት። የሕፃን ፊት። የሴት፥ የአዛውንትና የጎልማሳ ፊት። ተስፋን የሚናፍቅ ነገር ግን ተስፋው ጨርሶ የመነመነ ፊት። የሐዘንና የብቸኝነት ጥላ ያጠላበት ፊት። የሰብዓዊ ፍጡር ፊት። ኢትዮጵያዊ ፊት። የሕይወት ዕቅዱ በዓመታት፥ በወራት፥ ወይም በሳምንታት ውጥን ላይ የተመሠረተ ሳይሆንበሰዓታትና በዕለት ጉርስ ላይ ያተኮረ ፊት። የሚያጠግብ ሳይሆን እስትንፋስን የሚያቆይ፥ ጥም የሚቆርጥ ሳይሆን ጉሮሮን የሚያረጥብ ጠብታ ውሃ የሚናፍቅ ስብዕና ያለው ፊት። ሰብዓዊ መብትና ክብር የተነፈገው ፊት። ያ ኢትዮጵያዊ ፊት ነው በሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ፊቶች ተባዝቶ በጋዜጦችና በቴሌቭዥን የሚቀርብልን።

በዚያች የተረሳች የገጠር መንደር ውስጥ ያስተዋልኩት ልጅና የተጎሳቆለው የገጠር ኅብረተሰብ የረሀብንና የድህነትን አስከፊ ፊት ከሚያሳዩት የአገራችን እውነታዎች አንዱ ነው። ብዙውን ጊዜ ስለገጠር ስናስብ በአእምሮአችን የሚመጣው በልምላሜ ያጌጠ፥ ፀጥታንና ውበትን የተጎናፀፈ ስዕል ነው። ብዙውንም ጊዜ ይህ የአእምሮአችን ስዕል እጅግ አስቸጋሪ ሕይወት የሚመራውን የገጠር ኅብረሰተብ የዕለት ተዕለት የስቃይ ኑሮ ይጋርድብናል። የማከብራቸው ገጣሚ ደበበ ሰይፉ «ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ» ብለው በሰየሙት ሥነ ግጥም ውስጥ በውብ ቋንቋ እንደሚስሉት

ዓይነት ግርዶሽ። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በማዕከላዊው የሰሜን ኢትዮጵያ የግብርና ሕይወት ላይ ባተኮረው ሰፊና ጥልቅ የምርምር መፅሐፋቸው ውስጥ የኢትዮጵያን ገበሬ ኑሮ በተለይም ደግሞ የገጠሩን የምርት ሂደት፥ የገበያውን መዋቅርና አጠቃላይ የገጠሩን ኤኮኖሚ በስታትስቲክስ በማስደገፍ በሰፊው ይተነትናሉ። የኢትዮጵያ ገበሬ ለሶሽዮ ኤኮኖሚክስና ለፖለቲካዊ ሁኔታዎች እስረኛ እንደሆነ፥ ለሁኔታዎችም መፈጠር ወይም መለወጥ ምንም ሚና እንደሌለው፥ በአጠቃላይ ኑሮውን ለማሻሻል አማራጭና አቅም እንደተነፈገው የፕሮፌሰሩ ጥናት ያመለክታል። በኢትዮጵያ የግብርና ታሪክ ላይ መፅሐፍ የፃፈው ጄምስ ማካን ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር ተመሳሳይ የሆነ አመለካከት አለው። በኢትዮጵያ የፖለቲካም ሆነ የኤኮኖሚ ሂደት ታሪክ ውስጥ የገበሬው ደምፅአሳዛኝ በሆነ ደረጃ አናሳ መሆኑን ጄምስ ማካን ይገልፅና የኢትዮጵያ ገበሬ ድምፅ-አልባ ወይም «ዱዳ» ነው የሚል ማጠቃለያ ላይ ይደርሳል። ሀያ አንደኛውን ክፍለ ዘመን ጀምረነዋል። ነገር ግን (የከተማውን ድህነት እንዳለ ትተን) የኢትዮጵያ ገበሬ፥ በአጠቃላይም የገጠሩ ኅብረተሰብ አሁንም እንደተረሳ፥ አሁንም ድምፅ-አልባ እንደሆነ ይገኛል።

## ፪. ዛሬ

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለሚደርሰው ተደጋጋሚ የረሀብ አደጋ የተለያዩ ምክንያቶችን መስጠት ይቻላል። በመመጻደቅ የሕዝቡ ስንፍና ነው ከሚሉት አንስቶ በጥቅሉ የእግዚአብሔር ቁጣ ነው የሚል እምነት እስካላቸው ድረስ ብዙውን ጊዜ የሚደረደሩት ምክንያቶች ሚዛናዊ አይመስሉም። እኔ በግሌ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለተደጋጋሚ አስከፊ ረሀብ የዳረገውና የሚዳርገው ዋናው መንስኤ የተበላሸ የመንግሥት አስተዳደር ነው በሚለው አቋም እጸናለሁ። ኢትዮጵያ በሰው ኃይልም ሆነ በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ሆና ሳለ የሕዝቧን የረሀብ ስቃይ በተፈጥሮ ላይ ብቻ ማሳበብ አጥጋቢ ምክንያት አይሆንም። ተፈጥሮ ለረሀብ አስተዋጽኦ ቢያደርግም በተፈጥሮ የሚከሰቱ ችግሮች ከቁጥጥር ውጪ የሆኑ የረሀብ አደጋዎች እንዲያስከትሉ የምናደርገው እኛው ራሳችን ሰዎች ነን። የሕዝብን ሕይወትና የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽሉና ዋስትና የሚሆኑ ፍሬያማ የማኅበራዊ፥ የኤኮኖሚያዊ፥ የግብርና፥ የመሬት ይዞታ፥ የልማት፥ የውሃ አጠቃቀም፥ የኃይል ማመንጫ፥ የደንና የአፈር ጥበቃ፥ የትምሕርት እና የጤና ፖሊሲዎች ደካማነት አልፎም ጎጂነት ነው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያስርበው፥ የድህነቱንም ሰንሰለት የሚያጠብቀው። የኖቤል ሽልማት ተሸላሚው ኤኮኖሚስት አማርቲያ ሴን ረሀብን «የተዛባ የምግብ ባለመብትነት (ኢንታይትልመንት) የሚያስከትለው ሰው ሠራሽ ኤኮኖሚያዊ ቀውስ» በማለት ይገልጸዋል። ባለፉት ሠላሳ ዓመታት እንዳየነው ለሀገራችን ተደጋጋሚ ረሀብ መንስኤው በተፈጥሮ የሚከሰት ድርቅ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ ነው የሚቀርበው። ነገር ግን ድርቅም ሆነ ሌላ የአየር መዛባት የግድ ረሀብን ማስከተል እንደሌለበት ከሌሎች አገሮች ልምዶች መመልከት ይቻላል። ሕንድና ቻይና፥ እንዲሁም ቦትስዋና፥ ኬፕቨርዴ እና ኬንያ ረሀብን ለመከላከል ከወሰዷቸው ርምጃዎች ብዙ መማር ይቻላል።

ፍራንስስ ሙር ላፔ እና ጆሴፍ ኮሊንስ የዓለምን ረሀብ በተመለከተ «አስራ ሁለቱ ተረቶች» ብለው ባቀረቡት ጥናት ውስጥ አንዱ ተረት አድርገው በሁለተኛ ደረጃ የፈረጁት በተፈጥሮና በረሀብ መካከል አለ ስለሚባለው የተጋነነ ግንኙነት ነው። የድርቅ ክስተት ሁልጊዜ ረሀብ

እንደሚያስከትል ተደርጎ መታመኑ ትክክል እንዳልሆነ ፀሐፊዎቹ በማስረጃ አሳይተው፥ «ተፈጥሯዊውን የአየር ፀባይ ማንም ሊቀይር አይችልም። ነገር ግን የተመቻቸ የአየር ሁኔታና የተሻሻሉ ኤኮኖሚያዊ መዋቅሮችን በመዘርጋት ሕዝብ የምግብ ነፃነቱን እንዳይነፈግ ማድረግ ይቻላል»[1] የሚል አመለካከት ያቀርባሉ። ላፔና ኮሊንስ እንደ ምሳሌ አድርገው ካቀረቧቸው ማስረጃዎች አንዱ በ1980ዎቹ ዓመታት ከሰሃራ በረሃ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገሮች ላይ የደረሰውን ድርቅ ነው። በዚህ ድርቅ ከተጠቁት 31 ሀገሮች ውስጥ የረሀብ አደጋ የደረሰባቸው አምስቱ —ሞዛምቢክ፥ አንጎላ፥ ሱዳን፥ ቻድና ኢትዮጵያ— ብቻ እንደነበሩ ያስታውሱናል።

ማርቲን ራቫሊዮን ረሀብ «የመንግሥታትን ውድቀት አጉልቶ የሚያሳይ ክስተት» መሆኑን ይገልጽና ረሀብን የሚያስከትሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ድህነት፥ ደካማ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ መዋቅሮች፥ ግድየለሽና ዝግጁ ያልሆነ መንግሥታዊ አስተዳደርና ግልጽነትና ተጠያቂነት የጎደለው የፖለቲካ ሥርዐት እንደሆኑ ይገልጻል። አማርቲያ ሴንና ዣን ድሬዝ በጻፉት «ሃንገር ኤንድ ፓብሊክ አክሽን» በተሰኘው መፅሐፋቸው ውስጥ የሚከተለውን አስፍረዋል፤ «በእርግጥ ረሀብን በተፈጥሮ ላይ ማሳበብ እጅግ ቀላልና አመቺም ነው። በተለይም በሥልጣንና በሃላፊነት ላይ ለሚገኙ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ይህ ሰበብ ታላቅ ጠቀሜታ አለው። ነገር ግን እንደዚህ አይነቱ ቀላልና ምቹ የሆነ ሰበብ ብዙውን ጊዜ የሚሸመተው በከባድ ዋጋ ነው። ይህ ከባድ ዋጋም ሁልጊዜ የሚከፈለው አቅም፥ መብትና ድምፅ በሌላቸው የታፈኑ ዜጎችና በሕይወታቸውም ጭምር ነው።»

በ1980ዎቹ የተካሄደ አንድ ጥናት በዓለም ላይ ያለውን የረሀብ አደጋ አስከፊነት ለማስረዳት የሚከተለውን አስደንጋጭ ምሳሌ ተጠቅሞ ነበር፤ «በየዓመቱ በምግብ እጥረት ከሚሰቃየው አምስት መቶ ሚሊዮን የዓለም ሕዝብ ውስጥ አርባ ሚሊዮኑ በረሀብና ረሀብ በሚያስከትላቸው በሽታዎች ይሞታል። ለግንዛቤ እንዲረዳን በየዓመቱ የሚሞተውን አርባ ሚሊዮን ሕዝብ በመንገደኞች ብንመስለው ሙሉ ተሳፋሪዎች የጫኑና ከተሳፋሪዎቹም ውስጥ ግማሽ ያህሉ ሕፃናት የሆኑባቸው ከ300 በላይ የመንገደኛ ማመላለሻ ጃምቦ ጄት አውሮፕላኖች በየቀኑ የመከስከሳቸውን ያህል ነው።» ለመሆኑ በአሁኑ ወቅት የኤይድስ በሽታ ተጨምሮበት በረሀብና በንጹሕ ውሃ እጦት የሚያልቀው የሀገራችን ሕዝብ ቁጥር በስንት ጃምቦ ጄቶች ይተመን ይሆን?

በረሀብ ላይ ያተኮረውን ይህንን አጭር ፅሑፍ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ከምትገኝ የምንጭ ውሃ ዳር ቆሜ ያስተዋልኩትን በመተረክ የጀመርኩት ያለምክንያት አይደለም፤ ያቺ የምንጭ ውሃና ያ ትንሽ ልጅ ኢትዮጵያን ለረሀብ ያጋለጧትን ሁኔታዎች ቁልጭ አድርገው በምሳሌነት ስለሚያሳዩ እንጂ። ውሃ ቀጂው ልጅና ምንጯ ብዙ እውነታዎችን ያመላክታሉ። ውጤታማ የሆኑ የገጠር ልማት ፖሊሲዎች ሥራ ላይ አለመዋላቸውን፤ ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የገጠር ኅብረተሰብ ኑሮ ሁልጊዜም ለረሀብ፥ ለበሽታና ለእርዛት የተጋለጠ መሆኑን፤ የንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አለመኖር ሕዝቡን ለበሽታ ከማጋለጡ በተጨማሪ በየቀኑ ውሃ በማመላለስ የሚጠፋው ጊዜና ጉልበት በኅብረተሰቡ ኑሮ ላይ ከባድ ተጽእኖ እንዳለውና ሀገር ተረካቢ የሆኑ ሕፃናት በረሀብና

---

[1] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ለማስረጃነት ከምጠቅሳቸውና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከተጻፉት መጻሕፍት ውስጥ እየቀነጨብኩ ያቀረብኳቸውን ጥቅሶች ወይም ሀሳቦች በተቻለኝ መጠን ቃል በቃል ወይም ሀሳባቸው ሳይዛባ ወደ አማርኛ ለመተርጎም ሞክሬአለሁ። የትርጉም ግድፈት ካለ ሃላፊነቱ የራሴ ነው።

በድህነት የተነሣ በትምሕርት ታንጸው ምርታማ ዜጋ ለመሆን ያላቸው ዕድል እጅግ የመነመነ መሆኑን መመልከት ይቻላል። እነዚህና ሌሎችም አያሌ ውስብስብ ማኅበራዊ፥ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሲፈቱ ነው የረሀብ ሰንሰለቱም የሚበጠሰው። የተበላሹ የመንግሥት ፖሊሲዎች ሕዝብን ካለምንም መከላከያ አጋልጠው ስላስቀሩት ነው የረሀብ ጦር ደጋግሞ ሀገሪቱን የሚወጋት። ከአፈር ጋር ተቆራኝቶ የሚኖረው አርሶ አደርና ከብት አርቢ ኅብረተሰብ የእርሻና የእርባታ ዘዴውን እንዲያሻሽል፥ በመስኖ ውሃ በአግባቡ እንዲጠቀም፥ መጠባበቂያ እህል እንዲኖረው የሚያግዙት፥ በአጠቃላይ የመኖር አቅሙን ለማጎልበት የሚያስችሉት ሁኔታዎች እጅግ ውሱን ናቸው። እንዲያውም በአብዛኛው የገጠሩን ኅብረተሰብ በተለይም አርሶ አደሩን የሚያግዝ ሳይሆን የሚያዳክም ሁኔታና የአስተዳደር ሥርዐት ነው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው። ለምሳሌ ደቡብ ወሎ ውስጥ ያነጋገርኩዋቸው ገበሬዎች አንዱ ችግር መንግሥት እያስገደደ የሚያስገዛቸው ማዳበሪያ ጉዳይ ነው። ገበሬዎቹ ገንዘብ ሳይኖራቸው ማዳበሪያ በዕዳ እንዲገዙ መደረጉንና ክፍያውንም ከራሳቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጉርሻ እየነጠቁ ለመንግሥት እንደሚገብሩ ነበር ገበሬዎቹ በምሬት የነገሩኝ።

ረሀብ ገላን አመንምኖ፥ ስብዕናን አጎሳቁሎ፥ ሕሊናን አቁስሎ፥ ክብርን አጉድሎ፥ ተስፋን አጨልሞ፥ ልቡናን አሳዝኖ፥ ቤተሰብን በታትኖ የማለፉን ያህል በአንፃሩ ግን በአግባቡ የተዘጋጀን ኅብረተሰብ የመድፈር አቅም የለውም። ያልተዘጋጀን፥ የኢኮኖሚ ጉልበቱ ያልጠነከረን፥ ለ«ክፉ ቀን» የሚሆን ስንቅ ያላከማቸንና ኑሮውን በዕለት ጉርስ ላይ ብቻ የመሠረተን ኅብረተሰብ ግን አዳክሞ ለእልቂት ይዳርጋል።

በዚያች በተረሳች የገጠር መንደር ወዳየሁት ልጅ ልመለስ። ዕድሜው ከአስር ዓመት የማይበልጥ ታዳጊ ሕጻን በየቀኑ ለሰዓታት በእግሩ እየተጓዘ ውሃ በመቅዳትና በማመላለስ ከከባድ ሸክም ጋር ኑሮውን ይገፋል። ይህ ልጅ በሚሊዮኖች ከሚቆጠሩት በእርሱ ዕድሜና ተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ላይ ከሚገኙት ኢትዮጵያውያን ልጆች አንዱ ነው። ታዲያ የእርሱን ዓይነት ከባድ ኑሮ የሚገፋ ልጆች ቁጥር በሚሊዮኖች ከሆነ ኢትዮጵያ እንዴት ነው የምታድገው? ለለጋ እድሜ የሚገባውን እንክብካቤ፥ ምግብ፥ ንጹሕ ውሃና የቀለም ትምህርት የማያገኝ ትውልድስ እንዴት ነው ሀገሩን ሊገነባ፥ ሊያሳድግ የሚችለው? እነዚህ ጥያቄዎች በልተን የምንውለውን፥ ጠግበን የምናድረውን በተለይም ደግሞ በውጭው ዓለም የምንገኘውን ኢትዮጵያውያንን በእጅጉ ሊያሳስቡን ይገባል።

ኑሮ ለጨለመባቸው፥ ድምፅ ለሌላቸው፥ የተስፋ ጭላንጭል እንኳን ለተነፈጋቸው ወገኖቻችን፤ በተለይም ደግሞ በአያሌ ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሠራሽ ችግሮች የተዋጠውን የገጠር ኅብረተሰብ ማሰብ ከዚያም አልፎ ትርጉም ያለው እገዛ ማድረግ ዜጋዊም ሰብዓዊም ግዴታችን ነው። ጊዜያዊ እርዳታችን የወገኖቻችንን ሕይወት ማትረፉ አይቀርምና እጆቻችንን ከመዘርጋት ወደኋላ ማለት የለብንም። ይህንን ሰብዓዊ እርዳታችንን ሳናቋርጥ ለኢትዮጵያና ለተቸገረው ሕዝቧ ዘላቂ መፍትሔ ልናመጣ የምንችለው በሥራ ላይ ያሉትን ነገር ግን ከጠቀሜታቸው ይልቅ ጉዳታቸው የሚያመዝነውን ፖሊሲዎች ስንመረምርና ስንቀይር ወይም ደግሞ እንዲቀየሩ ድምፃችንን ማሰማት ስንችል ነው። የሕዝብን አቅም የሚያጎለብቱ በተለይም ደግሞ የገበሬውን ኑሮ የሚያሻሽሉና

ምርታማነቱንም ከፍ የሚያደርጉ ፖሊሲዎች ተነድፈው ሥራ ላይ እስኪውሉ ድረስ ድህነቱም፥ ረሀቡም፥ ችግሩም ይቀጥላል። የውሃ ቀጂው ልጅና የመሰሎቹም ሰቆቃ እንዲሁ[2]።

## ፫. ነገ

መጪው ዘመን ብሩህ የሆነ የዕድገት፥ የዕውቀት፥ የሰላምና የደስታ ዘመን እንዲሆን የሁላችንም ፍላጎት ነው። በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ፪ ሽህ ዓመተ ምሕረት ላይ ደርሰናል። የዘመን መለወጫ ዐውደ ዓመት ነውና ሁላችንም በያለንበት ከልባችን «እንኳን አደረሰን» እየተባባልን እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት፥ መልካም ምኞታችንንም የምንለዋወጥበት ቀን እነሆ ቀርቧል። ደስ ይላል፤ ባሕላዊም ታሪካዊም ይዘቱ የጎላ ነውና የዘመን መለወጫችን መስከረም ፩ ቀን ቤተሰባዊም፥ ማኅበራዊም፥ አገራዊም ቃና አለው። በዚህ በአዲሱ ዓመት ረሀብ ወደ ብልጽግና፥ ድርቅ ወደ ልምላሜ፥ ጭንቀት ወደ እፎይታ፥ መከራ ወደ ደስታ፥ ቂም በቀል ወደ ይቅርታ፥ መለያየት ወደ አንድነት፥ ክሕደት ወደ እምነት፥ ስስት ወደ ደግነት፥ ጥላቻ ወደ ፍቅር፥ ጥርጣሬ ወደ ጽናት፥ ስንፍና ወደ ትጋት፥ ትእቢት ወደ ትሕትና፥ ንቀት ወደ አክብሮት፥ ነቀፋ ወደ አድናቆት ተለውጦ የምናይበት እንዲሆን የሁላችንም ምኞት ነው። ይህ ሁሉ ምኞታችን እውን የሚሆነው አዲሱን ዓመት ለመቀበል ከምናደርገው ዝግጅት በበለጠ ራሳችንን ለመለወጥ ስንዘጋጅ ነው። እያንዳንዳችን «በአዲሱ ዓመት ወገኔን ከረሃብ ሰቆቃ ለማዳን ምን ለማድረግ ተዘጋጅቻለሁ?» የሚለውን ጥያቄ ራሳችንን የመጠየቅ፥ ለጥያቄውም መልሶቻችንን የማዘጋጀት ሃላፊነት አለብን። በዚህና በመሰል ጥያቄዎች ዙሪያ አጥጋቢ ምላሽ ይዘን ስንገኝ ብቻ ነው አዲሱን ዓመት ትርጉም ባለው መንገድ ለመቀበልና ለማክበር የምንችለው።

ከዚህ ውጪ ግን ሁለት ሽህ ዓመት ልንደፍን ነው ተብሎ «ሚሌንየም» በሚል ሽፋን በየቦታው እየተደረገ ያለው የፌንጠዝያና የአስረሽ ምቺው ዝግጅትና ትርዒት ለሚራብና ለሚቸገር ወገን ቅንጣት ያህል ለውጥ እንደማያመጣ አውቃለሁ። መስከረም ፩ ቀን ፪ ሽህ ዓ.ም. ለአገራችንና ለወገኖቻችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተፀምራዊ መፍትሔ ያመጣል ብዬም አልጠብቅም። እንዲያውም «ሚሌንየም» የሚባለው የባእድ ቃል ራሱ ለገጠሩ ኅብረተሰብም ሆነ ለችግረኛውና ለጎዳና ተዳዳሪው ከተሜ ምን ትርጉም እንደሚሰጠው ለመገመት ያስቸግረኛል። በተቃራኒው ለዚህ «ሚሌኒየም» ብለው ለሚጠሩት ወቅት ልዩ አቀባበል ለማድረግ እየተዘጋጁ ያሉ ወገኖች «በሽህ ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚመጣ» እንደሆነ በተደጋጋሚ ሲናገሩ እሰማለሁ። ለተራበ፥ ለተጠማ፥ ለታረዘና እስትንፋሱን ለማቆየት የዕለት ጉርስ ፍለጋ የችግር ኑሮ ለሚገፋው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እያንዳንዷ አዲስ ቀን በሽህ ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የምትመጣ፥ ተስፋንና ፍርሀትን በአንድ ላይ ያዘለች ብርቅ ቀን እንደሆነች እነዚህን ወገኖች ላስታውሳቸው እፈልጋለሁ።

---

[2] የወገን ነፍስ አድን ኮሚቴን በመወከል ለሶስተኛ ጊዜ ድርቅና ረሀብ ያጠቃቸውን የኢትዮጵያን የገጠር ክፍሎች ለመመልከት በተጓዝኩበት ወቅት ካጋጠሙኝ ልብ የሚነኩ አያሌ ገጠመኞች አንዱ የዛ ስሙን የማላውቀው ውሃ ቀጂ ትንሽ ልጅ ሁኔታ ነበር። በዚህኛው ጉዞ ከነጌሌ ቦረና አንስቶ ጅቡቲን እስከሚያዋስኑት ምሥራቃዊ የአፋር ወረዳዎች ድረስ የነበረውን የድርቅና የረሀብ ሁኔታ ተመልክቻለሁ። በሌላ ርዕስ ሰይሜው የነበረውን ይህንን ጽሑፍ ያዘጋጀሁት በግንቦት ወር ፲፱፻፺፮ ዓ.ም. ወይም በፈረንጆች ዘመን አቆጣጠር ሜይ 2004 ነበር።

ከሦስት ዓመታት በፊት ያየሁት ያ ውሃ ቀጂ ልጅ ዛሬ በግምት የአስራ ሦስት ወይም የአስራ አራት ዓመት ታዳጊ ወጣት ይሆናል — ረሀብና በሽታ ካልቀደሙት። በአውሬ መበላትም አለ (ድቅድቅ ባለው የገጠር ጨለማ በቡድን በቡድን እየሆኑ ከዋናው መንገድ ወጣ ብለው በእግራ ቸው ወደየጎጆቻቸው ሲጣደፉ እኔ በመኪና ያለፍኳቸው ብዛት ያላቸው ልጆችና ጎልማሶች ሁልጊዜ ትዝ ይሉኛል)። ዛሬ ወደዚያች የገጠር ምንጭ ተመልሼ ሄጄ ልጁ ውሃ ለመቅዳት ሲጋፋ ባየው ብዙም አይደንቀኝም። ይልቅ በሕይወትና በጤና መቆየቱ ይደንቀኝ ይሆናል። ባጋጣሚ ግን ባየው ወይም ባነጋግረው «እንኳን ለሚሌንየም አደረሰህ» ለማለት ድፍረቱ እንደማይኖረኝ አውቃለሁ። ምን አደረግሁለትና? በእግዚአብሔር ቸርነት ለአዲሱ ዓመት በመድረሱ ደስ ቢለኝም ኑሮው እንዲሻሻል ስላላገዝኩት፥ ከሸክሙም ስላላሳረፍኩት የኔ ባዶ «ሚሌንየም» ምን ሊጠቅመው? አዎ፤ የወገኖቻችንን ረሀብ፥ ጥም፥ እርዛት፥ ሕመም፥ ድህነት እና ጥቃት የራሳችን አድርገን እስካልወሰድን፥ ለመፍትሔዎቻቸውም የግልም የጋራም አስተዋጽኦ እስካላደረግን ድረስ ሽህ «ሚሌንየም» ቢመጣና ቢሄድ ለአገራችን ልማትና ዕድገት ለውጥ አያመጣም።

በዚህ «ሚሌንየም» ተብሎ በተመሰቃቀለ ስሜት በሚጠበቀው ወቅት ዋዜማም ሆነ ማግስት ለራሳችንም፥ ለአገራችንም፥ ለወገናችንም ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት፥ በተለይም ደግሞ ረሀብን ለማስወገድ ቃል የምንገባ ከሆነ፥ ቃላችንንም ወደ ተግባር ለመለወጥ የሩቅ ትልም ተልመን፥ የጋራ ራዕይ ቀርጸን በአንድነት የምንነሣ ከሆነ ግን እውነትም አዲስ ዘመን፥ እውነትም አዲስ ምዕራፍ ብለን ፪ ሽህን እንዘክረዋለን። በዚህም ረገድ በአዲሱ ፪ ሽህ ዓመተ ምሕረት ሁላችንም በያለንበት ለአገራችንና ለወገኖቻችን የምናበረክተው አንድ ታላቅ ስጦታ፥ አንድ ታላቅ ገጸ በረከት አለ . . . ራሳችንን። ስለሆነም ለአገርና ለወገን ልዩ ስጦታ፥ ልዩ ገጸ በረከት ለመሆን ራሳችንን እናዘጋጅ። ለዚያ ለውሃ ቀጂው ትንሽ ልጅ የልጅነት ሳቅ፥ የተስፋ ፈገግታ፥ የብሩህ ዘመን ራዕይ ምን እንደሆነ እናሳየው። አዎ፥ የአዲሱ ዓመት ልዩ ገጸ በረከት አድርገን ራሳችንን እናቅርብ። ነገን ከትናንቱና ከዛሬው የተሻለ ለማድረግም የርኅራኄ፥ የደግነትና የአርቆ አስተዋይነት ገጸ በረከት፥ የአለኝታነት ስጦታ እናበርክትላቸው . . . ለውሃ ቀጂው ትንሽ ልጅና ለአገራችን። እንችላለን! በእርግጥ እንችላለን።

---

ቴዎድሮስ አበበ
ስፕሪንግፊልድ፥ ቨርጂኒያ
ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም. (August 29, 2007)